# የኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር የዓቃቤ ሕግ ፈተና

## Part I: Choice (1% Each)

**1.** የለም

**2.** የለም

**3. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ውስጥ የተካተቱት መሰረታዊ መርሆዎች የትኞቹ ናቸው?**

- ሀ/ የህዝቦች የሉዓላዊነት መርህ
- ለ/ ፌደራሊዝም
- ሐ/ የሥልጣን መለያየት
- መ/ መሰረታዊ የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ
- ሠ/ ሀ እና ለ መልስ ናቸው
- ረ/ ሀ እና መ መልስ ናቸው

**4. የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት የዳኝነት ነፃነትን የመጠበቂያ መንገድ አድርጎ ያልደነገገው የትኛውን ነው?**

- ሀ/ የዳኝነትን ሥልጣን ለፍርድ ቤቶች ብቻ በመስጠት
- ለ/ ዳኞች ከውጫዊ ተጽእኖ ነፃ ሆነው የሚመሩበትን የአሰራር እና ሹመት ሁኔታዎችን በመዘርዘር
- ሐ/ የዳኞች የሥራ ነፃነት
- መ/ የፍርድ ቤቶች የበጀት ነፃነት
- ሠ/ ለዳኞች ያለመከሰስ መብት በመስጠት

**5. ከሚከተሉት መካከል በየትኛውም ሁኔታ ተለዋጭ ያልሆነ መብት የትኛው ነው?**

- ሀ/ የሕይወት፣ የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት
- ለ/ የክብርና የመልካም ስም መብት
- ሐ/ የግል ህይወት የመከበርና መጠበቅ መብት
- መ/ የልማት መብት
- ሠ/ መልስ አልተሰጠም

**6. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት መሰረት ልዩ የሆነው የቱ ነው?**

- ሀ/ የብሔራዊ ምክክር ቤት ኮሚሽን
- ለ/ የህዝብ ቆጠራ ኮሚሽን
- ሐ/ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን
- መ/ የእምባ ጠባቂ ተቋም

**7. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ መሰረት የገንዘብ መቀጮ ራሱን ችሎ እንደ አንድ ቅጣት እንዲወሰን አይፈቅድም።**

- ሀ/ እውነት
- ለ/ ሐሰት

**8. የፍትሐብሔር ህግን በወንጀል ህግ የአናሎጂ (Analogy) ትርጉም በህግ የተከለከለ አይደለም።**

- ሀ/ እውነት
- ለ/ ሐሰት

**9. __________________ ማለት አንድ ድርጊት ወይም ግድፈት በህግ ከአንድ በላይ ወንጀሎችን የሚያካትትበትን ሁኔታ ያመለክታል። እንደዚህ ባሉ አጋጣሚዎች ወንጀለኛው ከአንድ ድርጊት ወይም ጥፋት በተፈጠሩ በርካታ ወንጀሎች ሊከሰስ እና ሊፈረድበት ይችላል።**

- ሀ/ ከባድ ወንጀል
- ለ/ ልዩ ወንጀል
- ሐ/ ተደራራቢ ወንጀሎች
- መ/ ቀላል ወንጀል

**10. ታስቦ ሲፈጸም በወንጀል የሚያስቀጣ ድርጊት ሁሉ በቸልተኝነት ቢፈፀም በወንጀል ያስጠይቃል።**

- ሀ/ እውነት
- ለ/ ሐሰት

**11. በወንጀል አባሪነት ምን ጊዜም ቢሆን ታስቦ የሚፈፀም ተግባር ነው።**

- ሀ/ እውነት
- ለ/ ሐሰት

**12. ማንኛውም ወንጀል ሲፈፀም ያየ ሰው ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ የህግ ግዴታ አለበት።**

- ሀ/ እውነት
- ለ/ ሐሰት

**13. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ህግ መሰረት በአንድ ወንጀል ድርጊት በአባሪነት የተካፈለ ሰው የወንጀል ተጠያቂነትን አስመልክቶ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?**

- ሀ/ የወንጀል ድርጊት አድራጊ መሆን ማለት አንድ የወንጀል ድርጊት ላይ ከአንድ በላይ ሆነው በቀጥታ ድርጊቱን የፈፀሙ ሰዎችን የሚመለከት ነው
- ለ/ በአንድ በቸልተኝነት በተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ላይ ሁለት ሰዎች ተካፍለው ቢገኙ አንዱ ለሌላው አሳሪ ሊባል ይችላል
- ሐ/ ሁለት ሰዎች አንድ ወንጀልን ለመፈጸም በመሰናዳት ተግባር ላይ እያሉ ቢደረስባቸው ሁለቱም አባሪ ተደርገው ሊጠየቁ ይገባል
- መ/ ሀ እና ሐ ትክክል ናቸው
- ሠ/ ሁሉም ትክክል ነው
- ረ/ መልሱ የለም

**14. በልዩ ሁኔታዎች መሰረት የአንድ ተጠርጣሪ ሰው የአካል ነጻነት መብት ያለ ፍርድ ቤት የመያዣ ትዕዛዝ ሊገደብ የማይችለው:**

- ሀ/ በጸረ ሽብርተኝነት አዋጅ መሰረት የሚታዩ ወንጀሎችን ፈፅሟል ተብሎ ከተጠረጠረ
- ለ/ የአደገኛ ቦዘኔነትን ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ ጥሶ ሲገኝ
- ሐ/ የአካል ነጻነት መብትን ያለፍርድ ቤት የመያዣ ትዕዛዝ የሚገድብ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሲታወጅ
- መ/ የእጅ ተፍንጅ ወንጀል ፈጽሞ ሲገኝ
- ሠ/ መልስ አልተሰጠም

**15. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ በኢትዮጵያ የወንጀል ነክ ሂደት ደረጃዎች ውስጥ አይካተትም**

- ሀ/ የክስ ደረጃ
- ለ/ የምርመራ ደረጃ
- ሐ/ የመሰማት ደረጃ
- መ/ መልስ አልተሰጠም

**16. ክስ ለማቅረብ አጠራጣሪ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ ዐቃቤ ህግ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርዓት መሰረት ምን ማድረግ አለበት?**

- ሀ/ በቂ ማስረጃ አልቀረበም በሚል በወ/መ/ህ/ሥ/ቁ 42(1) (ሀ) መዝገቡን መዝጋት
- ለ/ ለፍርድ ቤት በማቅረብ በፍርድ ቤት እንዲወሰን ማድረግ
- ሐ/ በወ/መ/ህ/ሥ/ቁ 38(ሐ) መሰረት ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ ማዘዝ
- መ/ መልስ አልተሰጠም

**17. ማንኛውም መርማሪ አካል ከወንጀል ምርመራ ጋር ተያያዥ በወንጀል ህግ የሚሰጡ ትዕዛዞችን እና ምላሾችን ተቀብሎ የመፈፀም እና የማስፈፀም ግዴታ ይኖርበታል።**

- ሀ/ እውነት
- ለ/ ሐሰት

**18. ለተከሳሽ በጋዜጣ ጥሪ መጥሪያ የማድረስ ስርዓት በፍትሐ ብሔር ጉዳይ ላይ ብቻ የሚተገበር ነው።**

- ሀ/ እውነት
- ለ/ ሐሰት

**19. በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 130 ስር የተዘረዘሩት የመመርመሪያ ጊዜ መርማሪው የክስ መቃወሚያ ለማቅረብ አይችልም።**

- ሀ/ እውነት
- ለ/ ሐሰት

**20. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ መሰረት የወንጀል ምርመራን የመምራት እና የማስተባበር ኃላፊነት የ______________________ ነው።**

- ሀ/ የፍርድ ቤቶች
- ለ/ የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ
- ሐ/ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን
- መ/ የብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት
- ሠ/ ከላይ የተጠቀሱት አካላት በሙሉ በጋራ ይመሩታል

**21. በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ መሰረት በወንጀል ጉዳይ ማረጋገጥ ከሚፈለገው ፍሬ ነገር አንፃር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌለው ማስረጃ ተቀባይነት የለውም።**

- ሀ/ እውነት
- ለ/ ሐሰት

**22. የወንጀል ክስ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜን አስመልክቶ በተከሳሽ የክስ መቃወሚያ ሳይቀርብ ፍርድ ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት ለመወሰን አይችልም።**

- ሀ/ እውነት
- ለ/ ሐሰት

**23. ከሚከተሉት የፍትሐብሔር ክርክሮች ውስጥ የይርጋ ዘመን የሌለው የክስ ምክንያት የትኛው ነው?**

- ሀ/ በሽያጭ ውል ግንኙነት ምክንያት
- ለ/ የውርስ ክርክር
- ሐ/ በአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ምክንያት
- መ/ የባለቤትነት መብት ለማረጋገጥ ግንኙነት ምክንያት

**24. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ትክክለኛው የቱ ነው?**

- ሀ/ ውሎች ውጤት የሚኖራቸው በተዋዋይ ወገኖች ላይ ነው የሚለው መርህ (principle of privity) ልዩ ሁኔታ (exception) የለውም።
- ለ/ ተዋዋይ ወገኖች የሚገቡት በግልጽ በተስማሙበት ግዴታ ላይ ብቻ ሳይሆን ከግዴታው ጋር ተያይዘው የሚመጡ ከልማድ፣ ቅን ልቦና እና የውለታው ዓይነት የሚስከትሏቸውን ነገሮች ጭምር ነው።
- ሐ/ የአመሰራረት ጉድለት ያለበት ውል ምንም አይነት ውጤት የሌለው (void ab initio) ነው።
- መ/ በኢትዮጵያ የውል ህግ የተለየ የውል ቅርፅ (special form/written form) መከተል ሁልጊዜ አስፈላጊ ነው።

**25. ከሚከተሉት ትክክል የሆነው የትኛው ነው?**

- ሀ/ የግልገል ዳኝነት ከፍ/ቤት የሚሻለው የጉዳዩ ሂደት በተከራካሪ ወገኖች ፍላጎት እና ስምምነት ስለሚመራ ነው።
- ለ/ የፍርድ ቤት ክርክር ከግልገል ዳኝነት ጋር ሲወዳደር ወጪ ቆጣቢ ነው።
- ሐ/ ዓለምአቀፍ ጉዳዮችን በተመለከተ የፍርድ ቤት ውሳኔ ከግልገል ዳኝነት ውሳኔ የበለጠ ተፈፃሚነት አለው።
- መ/ የግልገል ዳኝነት ስርዓት ልክ እንደ ፍ/ቤት ሁሉ ራሱን ችሎ የቆመ ምሉዕ የሆነ የግጭት መፍቻ ስርዓት ነው።

**26. በኢትዮጵያ የውል ህግ የኪሳራ አቆራረጥን በተመለከተ ትክክለኛው የቱ ነው?**

- ሀ/ የሚከፈለው ኪሳራ አዕምሮ ያለው ሰው ውል ባለመፈፀሙ ይደርሳል ብሎ የሚገምተው አስተያየት ልክ ነው።
- ለ/ የሚከፈለው ኪሳራ ውሉ ባለመፈፀሙ በሌላው ወገን በደረሰበት ጉዳት ልክ ነው
- ሐ/ የሚከፈለው ኪሳራ ውሉ ቢፈፀም ኖሮ ሊገኝ ይችል የነበረ ትርፍን፣ የገበያ አማራጭን እና ሌሎችን ይጨምራል።
- መ/ ሁሉም መልስ ነው።

**27. ፍትህ ሚኒስቴር የመንግስት ተቋማት እርስ በርስ የፍትሐብሔር አለመግባባቶችን ሲነሱ የመወሰን ስልጣን አለው።**

- ሀ/ እውነት
- ለ/ ሐሰት

**28. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የአሰሪና ሰራተኛ ህግ (Labour Proclamation) መሰረት አንድ አሠሪ አዲስ ተቀጣሪ ሰራተኛን ለምን ያህል ጊዜ በሙከራ ሊቀጥረው ይችላል? በዓቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 443/2011 መሰረትስ?**

- ሀ/ በቅደም ተከተል ለ30 የስራ ቀናት እና ለ3 ወራት
- ለ/ በቅደም ተከተል ለ30 የስራ ቀናት እና ለ6 ወራት
- ሐ/ በቅደም ተከተል ቢበዛ 45 የስራ ቀናት እና ለ6 ወራት
- መ/ በቅደም ተከተል ቢበዛ 60 የስራ ቀናት እና ለ 6 ወራት
- ሠ/ በቅደም ተከተል ቢበዛ 60 የስራ ቀናት እና ለ 3 ወራት

**29. ከሀገራችን የህግ አወጣጥ ስርዓት አኳያ ከሚከተሉት ህጎች የተለየ የቱ ነው?**

- ሀ/ የንግድ ህግ
- ለ/ የፍትሐብሔር ህግ
- ሐ/ የአሰሪና ሰራተኛ ህግ
- መ/ የመሬትና የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ህግ

**30. በሙስና ወንጀል ሊጠየቁ የሚችሉት የመንግስት እና ህዝባዊ ድርጅቶች ሰራተኞች ብቻ ናቸው።**

- ሀ/ እውነት
- ለ/ ሐሰት

**31. የሙስና ወንጀል ምርመራ እና ክስን በዋናነት የሚያከናውነው ተቋም የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ነው።**

- ሀ/ እውነት
- ለ/ ሐሰት

**32. በሙስና ጉዳይ የተጠረጠረ ሰው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሊቀርብ አይችልም።**

- ሀ/ እውነት
- ለ/ ሐሰት

**33. ከሚከተሉት አንዱ በሙስና ወንጀል ሊከሰስ አይችልም**

- ሀ/ አስታራቂ ሽማግሌ
- ለ/ የመንግስት ሰራተኛ
- ሐ/ የባንክ ሰራተኛ
- መ/ መልስ አልተሰጠም

**34. ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አንዱ አሁን በስራ ላይ ባሉት ህጎች እና አስገዳጅ ትርጓሜዎች ዋስትና ለማስከልከል በቂ ምክንያት አይደለም።**

- ሀ/ በከባድ የሙስና ወንጀል መጠርጠር
- ለ/ በኮንትሮባንድ ወንጀል መጠርጠር
- ሐ/ ቢለቀቅ ሌላ ወንጀል ይፈጽማል ተብሎ የሚገመት ከሆነ
- መ/ ምስክሮችን ያባብላል ተብሎ የሚገመት ከሆነ

**35. ከእነዚህ መካከል አንዱ ወንጀል የተፈፀመበት ንብረት መውረስን የሚያስከትል ወንጀል አይደለም።**

- ሀ/ በወንጀል የተገኘ ሀብት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ
- ለ/ ምንጩ ያልታወቀ ሀብትና ገንዘብ መያዝ
- ሐ/ ፈቃድ ሳይኖር የውጭ ሀገር ገንዘብ ይዞ መገኘት/መሸጥ/መመንዘር
- መ/ ደረሰኝ አለመቁረጥ
- ሠ/ መልስ አልተሰጠም

**36. ከእነዚህ መካከል ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?**

- ሀ/ በንግድ ውድድር ላይ የጎላ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያስከትል ስምምነት በህግ ተከልክሏል፡፡
- ለ/ ሸማች በአንድ እቃ ላይ ድርድር በማድረጉ ምክንያት እቃውን እነዲገዛ አይገደድም፡፡
- ሐ/ ማንኛውም ነጋዴ የዕቃ/አገልግሎት ዋጋ ሲያመለክት የታክስ እና ሌሎች ሕጋዊ ክፍያዎችን መረጃዎችን ሳያካትት ማሳወቅ ይችላል፡
- መ/ መሰረታዊ ፍጆታዎችን በተመለከተ የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ዝርዝራቸውን፣ የሥርጭት መስመራቸውንና ዋጋቸውን በህዝብ ማስታወቂያ ይወሰናል፡፡

**37. ከሚከተሉት መካከል አንዱ ቀጥታ ታክስ አይደለም፡፡**

- ሀ/ ተጨማሪ እሴት ታክስ
- ለ/ የንግድ ስራ ገቢ ግብር
- ሐ/ ዊዝሆልዲንግ ታክስ
- መ/ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር

**38. በአስተዳደር ስነ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሠረት የአስተዳደር ተቋም ያልሆነው የቱ ነው?**

- ሀ/ ፍትህ ሚኒስቴር
- ለ/ ፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
- ሐ/ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን
- መ/ ትምህርት ሚኒስቴር
- ሠ/ ለ እና ሐ

**39. የሀገራችን የሕግ ማዕቀፍ አካል ያልሆነው የቱ ነው?**

- ሀ/ የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን
- ለ/ የዓለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት ስምምነት
- ሐ/ ሽብርተኝነትን ለመከላከልና ለመዋጋት በአፍሪካ አንድነት ድርጅት የወጡ ኮንቬንሽኖች
- መ/ የተደራጁ ድንበር-ዘለል ወንጀሎችን ለመከላከል የተደረሰ ስምምነት
- ሠ/ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን
- ረ/ መልስ አልተሰጠም

**40. በኢትዮጵያ በወንጀል ጉዳዮች ዓለም አቀፍ ግንኙነትና ትብብር ማድረግ የቅድሚያ ተሰጥኦ ተግባርና ኃላፊነት ነው?**

- ሀ/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
- ለ/ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን
- ሐ/ የፍትህ ሚኒስቴር
- መ/ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች

**41. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው የህግ ትርጉም በየትኛውም ፍርድ ቤት አስገዳጅነት የሚኖረው ከመቼ ጀምሮ ነው?**

- *ሀ/ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ*
- *ለ/ ውሳኔው በህትመት ሚዲያ ከታተመበት ቀን ጀምሮ*
- *ሐ/ ውሳኔው በፍርድ ቤቱ ዌብሳይት ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ከተሰራጨበት ቀን ጀምሮ*
- *መ/ ባለጉዳዮች የወሰነውን ግልባጭ ከወሰዱበት ቀን ጀምሮ*
- *ሠ/ ውሳኔው በህትመት ሚዲያ ከተሰራጨበት ቀን ጀምሮ*

**42. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በወክልና የሚያዩት የፌዴራል ጉዳይን በተመለከተ ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ አቤቱታ የሚቀርበው ለየትኛው ፍርድ ቤት ነው?**

- *ሀ/ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት*
- *ለ/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት*
- *ሐ/ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት*
- *መ/ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት*
- *ሠ/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት*

**43. በውጭ ሀገር የተፈፀመ ወንጀልን በሚመለከት የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ምትክ ስልጣን (subsidiary jurisdiction) እንጂ ዋና ስልጣን (principal jurisdiction) ሊኖራቸው አይችልም፡፡**

- *ሀ/ እውነት*
- *ለ/ ሐሰት*

**44. ፍትህ ሚኒስቴር የወንጀልና የፍትሐ ብሔር ህግን እንጂ የአስተዳደር ህግን የማስፈጸም ስልጣንና ተግባር የለውም፡፡**

- *ሀ/ እውነት*
- *ለ/ ሐሰት*

**45. ፍትህ ሚኒስቴር ህጎችን በማስፈጸም ረገድ ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ ውጭ በክልሎች ማንኛውንም ህግ የማስፈጸም የአካባቢ ስልጣን (Local Jurisdiction) የለውም፡፡**

- *ሀ/ እውነት*
- *ለ/ ሐሰት*

**46. በህግ የተቋቋሙ የመንግስት ተቋማት ፍትሐብሔራዊ በሆኑ ጉዳዮች በስማቸው የመክሰስም ሆነ የመከሰስ ስልጣን ያላቸው እንደመሆኑ የፍትህ ሚኒስቴር ኃላፊነት ድጋፍ በማድረግ ብቻ የተገደበ ነው፡፡**

- *ሀ. እውነት*
- *ለ. ሐሰት*

**47. በወንጀል ፍትሕ ስርዓት ሂደት የዐቃቤ ህግ ስልጣን ያልሆነው የቱ ነው?**

- ሀ/ የወንጀል ክስ አቤቱታ መቀበል
- ለ/ የወንጀል ምርመራ መምራት
- ሐ/ ኤግዚቢት ላይ መወሰን
- መ/ የጥፋተኝነት ድርድር ማድረግ
- ሠ/ መልስ የለም

**48. በአስተዳደር ስነ ስርዓት አዋጅ 1183/2012 መሰረት ፍትሕ ሚኒስቴር እንዲመዘግብ ኃላፊነት የተሰጠው የቱን ነው?**

- ሀ/ ደንቦችን
- ለ/ የአስተዳደር ተቋማት መመሪያዎችን
- ሐ/ የተቋማት አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን
- መ/ ሁሉም

**49. የዲሲፕሊን ክስ የቀረበበት ማንኛውም ዐቃቤ ህግ ጉዳዩ ታይቶ ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ ከስራና ከደመወዝ ታግዶ ይቆያል፡፡**

- ሀ/ እውነት
- ለ/ ሐሰት

**50. በዐቃቤያነ ህግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 443/2011 መሰረት ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ያልሆነው የቱ ነው?**

- ሀ/ ጉቦ መቀበል
- ለ/ የስራ ባልደረባን በሀሰት መወንጀል
- ሐ/ በስራው ላይ ተግቢ ትጋት አለማሳየት
- መ/ ሰክሮ በስራ ላይ መገኘት

**51. አንድ ሰው በፍትሕ ሚኒስቴር ውስጥ ዐቃቤ ህግ ሆኖ ተሹሞ በሥራ ላይ እያለ ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ተመድቦ ሊሰራ ይችላል፡፡**

- ሀ/ እውነት
- ለ/ ሐሰት

**52. አንድ ዐቃቤ ህግ በጽሁፍ ወይም በቃል ከመስሪያ ቤቱ ወይም ከቅርብ ኃላፊው ወይም ከበላይ ኃላፊ የተሰጠው ማንኛውም ዓይነት ትዕዛዝ ካልፈጸመ በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ይጠየቃል፡፡**

- ሀ/ እውነት
- ለ/ ሐሰት

**53. የሙከራ ጊዜን ያላጠናቀቀ ዐቃቤ ህግ በልዩ ሁኔታ ለ__________ ጊዜ በሥራ ገበታው ላይ ካልተገኘ ያለ ተጨማሪ ስነ ስርአት አገልግሎት ይቋረጣል፡፡**

- ሀ/ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት
- ለ/ ለ15 ተከታታይ የስራ ቀናት
- ሐ/ ለ30 ተከታታይ የስራ ቀናት
- መ/ ለ45 ተከታታይ የስራ ቀናት

## Part II: Short Answer & Listing

**54. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግሥት መሰረት በማንኛውም ሁኔታ የማይገደቡ መብቶችን ይዘርዝሩ (3 ነጥብ)።**

**55. በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላት የወንጀል ተጠያቂነት መመስረቻ ቅድመ-ሁኔታዎች መካከል ሦስቱን ይጥቀሱ (3 ነጥብ)።**

**56. በወ/መ/ስ/ህ መሰረት የፖሊስ ሪፖርት የደረሰው ዐቃቤ ህግ ማድረግ ከሚገባው ውስጥ ሁለቱን ይጥቀሱ (2 ነጥብ)።**

**57. በወ/መ/ስ/ህ መሰረት የክስ ማመልከቻ ላይ ሊጠቀሱ የሚገባቸው 4 ነገሮች ይዘርዝሩ (4 ነጥብ)።**

**58. በወ/መ/ስ/ህ መሰረት የወንጀል ክስ የማያቀርብባቸውን ሦስት ሁኔታዎች ይዘርዝሩ (3 ነጥብ)።**

**59. Mention at least three objections to a criminal charge (3 pts)**

**60. ውል እንዲፈጸም ማስጠንቀቂያ መስጠት ጠቃሚ የማይሆንባቸውን (Notice when unnecessary) አራት ምክንያቶች ይዘርዝሩ (4 ነጥብ)።**

**61. በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ መሰረት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተብለው ከተዘረዘሩት መካከል አምስቱን ይጥቀሱ (5 ነጥብ)።**

**62. በውል የተገባ ግዴታ ቀሪ ሊሆን ከሚችልባቸው ምክንያቶች መካከል አራቱን ይጥቀሱ (4 ነጥብ)**

**63. በኢትዮጵያ የውል ህግ ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል አለ የሚያሰኙ አራት ምሳሌዎች ይጥቀሱ (4 ነጥብ)**

**64. Mention two grounds for termination of a treaty (2 pts)**

**65. ለፍትሕ ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ ሦስት ተቋማትን ይዘርዝሩ (3 ነጥብ)**

**66. በዐቃቤ ህግነት ሙያ ውስጥ ከሚከለከሉ ሁኔታዎች ውስጥ አራቱን ይጥቀሱ (4 ነጥብ)**

**67. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግሥት መሰረት ሃይማኖት እና እምነትን የመግለጽ መብት ሊገደብ ከሚችልባቸው ልዩ ሁኔታዎች መካከል ሶስቱን ጥቀሱ (3 ነጥብ)**